ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ት/ጽ/ 5/16
ቀን 08/05/2016 ዓ.ም

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ት/ት/ጽ/ቤት

*ለሁሉም የመንግስት እና የግል 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሙሉ*

አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፡- <u>በተቋማችሁ ውስጥ ላሉ መምህራን እና አስተዳደር ሰራተኞች እንድታሳውቁ ስለመግለጽ</u>

ከላይ በርእሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በቁጥር አ11/9641/አ28-40/35 በቀን 03/05/2016ዓ.ም በጻፈልን ደብዳቤ ጤግሮስ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል/ ማህበር የትብብር ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው አሳውቆናል ፡፡ በዚህም መሰረት ጤግሮስ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል/ ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ የመንግስት እና የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ና ሰራተኞችን **ደራሽ ልዩ የመኪና እና የጤና ሽፋን** ስጦታ ለመስጠት እና የመኪና ተጠቃሚ ለማድረግ በ2ኛ ዙር የ40/60 በሚል ፕሮግራም በማዘጋጀት በአነስተኛ ቁጠባ እና በረጅም ጊዜ የክፍያ መንገድ በማመቻቸት ምዝገባ የጀመረ እንደሆነና ይህንንም ተግባር በፋይናስ እንዲያግዘን ህጋዊ ከሆነው በመንግስት እውቅና አግኝቶ ላላፉት ዓመታት በገንዘብ ቁጠባና ብድር አገልግሎት እየሰራ ከሚገኘው ፍኖት የገንዘብ ብድር ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር ጋር ሙሉ ስምምነት በማድረግ ተመዝጋቢዎች የሚያስቀምጡትን ቁጠባ በማስቀመጥ እና 40/60 ብድር እንዲሰጣቸው ተስማምተው እየሰሩ መሆናቸውንና የትብብር ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው የጠየቁ መሆናቸውን አጣቅሶ ገልጸልናል ፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ዓላማው መምህራንና የትምህርት አመራሩን የኢኮኖሚ አቅም የሚያሳድግና የመማር ማስተማሩን ስራ ውጤታማ ለማድረግ የራሱን አስተዋጽኦ ሊያበረክት የሚችል መሆኑ ስለታመነበት እና እንዲሁም የመንግስትን ግዴታ ለመወጣት ህጋዊ ፈቃድ ይዘው የሚንቀሳቀሱ መሆኑ ግምት ውስጥ በማስገባት በስራችሁ ላሉ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ስር ለሚገኙ መምህራን እና አስተዳደር ሰራተኞች ይህን እድል እንዲጠቀሙ ለማድረግ የድጋፍ/የትብብር/ ደብዳቤ ለየትምህርት ቤቶች እንድንጽፍ አሳውቆናል፡፡ ስለሆነም በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ እያስተማሩ ያሉ መምህራን ፣ የትምህርት አመራሮች እና የአስተዳዳር ሰራተኞች ይህን እድል አግኝተው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን እድል እንድታሳውቋቸው እያልን የአዲስ አበበ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የጻፈውን ደብዳቤ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እየገለጽን በእናንተ በኩል አስፈላጊውን ትብብር ታደርጉላቸው ዘንድ በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ከበደ ዲሪባ ኦልቀባ
Kebede Diriba Olkeba

ግልባጭ፡-

- በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ት/ጽ/ቤት